# ከታዘለ ደባ!

ከጌታቸው ቀጀላ

የግንባር ኩስትሪያ - የዓይን መፋጠጥ፤
ወኔ ይጠይቃል - ይዞ ማናፈጥ።
ቀድሞ ከድቶ ወኔ - ይኸኛው ከታጣ፤
ያም መጥፎ አልነበር! ህፃን መስሎ ታዝሎ ትግል በፍንጠጣ።
ወድቀው ላይላጡ፤ ቢሆን መታዘሉ፤
ያስመሰግን ነበር - ከጫንቃ መዋሉ።

በክንድ በጉልበቱ - ሽንጥ እየጎሸመ፤
ማጅራትን አንቆ - ይዞ እያሳመመ፤
ጆሮን ቁንጥጥ አርጎ - ጤናን እየነሳ፤
ከሆነ ሊያዘልል - ሊያሰኝ ደንገላሳ!

ፀጉርን ጭምድድ አርጎ - ራስ አስወዝውዞ፤
የልብን ሊያስደርስ - በጠላት አስፎዞ፤
ቢሆን ኖሮ ግቡ - እንዳንቀልባ ትግል የታለ ጨርሶ!
እወድቃለሁ ሳይሉ - ከስር ተሾልኮ፤ ከጎን ተፈትልኮ፤
ድቁስ አስደራጊ ከጀርባ ተላኮ።

ግና አይውልም ለዚህ፤ ፍርግጫው ቁንጥጫው፤
በቀላጅ ሲፈፀም ወገን ለማሳዘን፤ ወላጅ ለመጉዳት ነው።
የእናት መገለጫው፤ አንቀልባው ወገኔ፤
ለታዛዮች ሲውል - እሱ አልቆ በጠኔ።
የእሽኮኮን ለእሽኮኮ - ያንቀልባን ለአንቀልባ፤
ሽካፉን ያጅለው - ከታዘለ ደባ።

-----------------------